# የፐርፐዝብላክ ኢትዮጵያ

# ሳምንታዊ ጋዜጣ

Purpose Black ETHIOPIA

2015 ሰኔ ቅጽ 1 ቁጥር 17


## ፐርፐዝብላክ ኢትዮጵያ የኢኮሜርስ ዘርፉን በመላ ኢትዮጵያ በይፋ የሚያስተዋውቅበትን መርሐግብር አካሔደ።

ፐርፐዝብላክ ኢትዮጵያ በበይነ መረብ የሚያደርገውን ግብይት በተቀላጠፈ አሠራር ለማከናወን እና የተደራሽነት አድማሱን በመላ ኢትዮጵያ ለማስፋት የሚያስችለውን ዝግጅት አጠናቅቆ "ሁሉም ነጋዴ፣ ሁሉም አከፋፋይ ሁሉም ሠራተኛ" በሚል መፈክር ማንኛውም ሽያጭ እና ግዢ የሚከናወንበት ሁለገብ መገበያያ መርህ እንደሚሆን ለጋዜጠኞች በሰጠው መርሐግብሩን የተመለከተ ጋዜጣዊ መግለጫ ይፋ አድርጓል።

ሰኔ 24 ቀን 2015 ዓ.ም በኩባንያው ዋና መሥሪያ ቤት የተካሔደው ይህ ሁነት ከጠዋቱ 3፡00-7፡00 ሰዓት ድረስ የዘለቀ ሲሆን በአጠቃላይ 150 የሚጠጉ እንግዶች ታድመውበታል።

ምስል በ ጌታባለው ገ/ሃና



"

**የፐርፐዝብላክ ኢትዮጵያ ዋና ሥራ አስፈጻሚ ዶ/ር ፍስሐ እሸቱ የእንኳን ደኅና መጣችሁ መልእክት አስተላልፈው ባስጀመሩት በዚህ መርሐግብር ይህ የኢኮሜርስ ሥርዓት በአገራችን ያለውን የበይነመረብ ግብይት ካለበት ደረጃ ወደ ላቀ ከፍታ ከማሳደጉም በላይ በመላው አፍሪካ እና ጥቁር ማኅበረሰብ ዘንድ ተደራሽ መሆን የሚችል ከዚያም ባለፈ ዓለም አቀፍ ተወዳዳሪ የሆነ አገር በቀል የኦንላይን መገበያያ አማራጭ እንዲሆን እንደታለመ ተናግረዋል።**


ዋና ሥራ አስፈጻሚው አክለውም በዛሬው ዕለት በይፋ የተጀመረው የኢኮሜርስ ሥርዓት ዘመናዊ ቴክኖሎጂን የተከተለ፣ ሕይወትን ቀላል የሚያድርግ፣ እና ጊዜ እና ጉልበትን በእጅጉ የሚቆጥብ ከመሆኑ ባለፈ አገራችን ኢትዮጵያ እንደ ዲጂታል ኢትዮጵያን እውን ማድረግ፤ ካሸለስ ማኅበረሰብ፤ የሥራ ዕድል መፍጠር፤ የኅብረተሰባችንን የነፍስ ወከፍ ገቢ ከፍ ማድረግ እና ጠቅለል ሲደረግ መካከለኛ ገቢ ካላቸው ሀገሮች ተርታ መሰለፍ በሚል የያዘቻቸውን ውጥኖቿን እውን ለማድረግ ያግዛል ሲሉ ጠቀሜታውን አብራርተዋል፡፡

ምስል በ ኤደን ደነቀ



ሁሉም አከፋፋይ፣ ሁሉም ነጋዴ፣ ሁሉም ሠራተኛ በሚል መርሕ የተጀምረው ይህ ታላቅ አገራዊ ፋይዳ ያለው ፕሮጀክት ስያሜው የከገበሬው ብሔራዊ ወኪል ምርት ማከፋፈል አገልግሎት ሲሆን ከዚህ በፊት አገልግሎት ሲሰጥ በቆየው ኢኮሜርስ ሲሠራበት ከነበረው የግብርና እና የምግብ ምርቶችን ከማከፋፈል በተጨማሪ ሁሉንም ዓይነት ውጤቶች ማለትም የግብርና እና የማቀነባበሪያ ምርቶች፣ ኤሌክትሮኒክሶች፣ ፈርኒቸሮች፣ የሕጻናት እና አዋቂዎች አልባሳት፣ መድኃኒቶች፣ የፋብሪካ ውጤቶች፣ እና የእንስሳት ተዋጽዖዎችን፣ በአገር አቀፍ ደረጃ ለማከፋፈል ያለመ መሆኑም በሁነቱ ተገልጿል።

ምስል በ ኤደን ደነቀ




"

**የጦር መሣሪያ እና አደንዛዥ እጾችን ከመሳሰሉት ለሰው ልጅ ጎጂ እና አላስፈላጊ ከሆኑ ፍጆታዎች ውጪ ያሉትን ሁሉንም ምርቶች ለማከፋፈል ቅድመ ዝግጅቶች መጠናቀቃቸውን ያስታወቁት ዶ/ር ፍስሐ እሸቱ ይህንን ፕሮጀክት ተግባር ላይ ለማዋል ወጣቶች እና ሴቶችን እንዲሁም የከገበሬው ወኪል አከፋፋዮችን ማእከል ማድረጉንም አንሥተው በአዲስ አበባ ብቻ አንድ ሺህ ወኪል አከፋፋዮችን እና 10 ሺህ ወጣቶች እና ሴቶችን በክልል ከተሞች ደግሞ ዘጠኝ ሺህ ወኪል አከፋፋዮችን እና 40 ሺህ ወጣቶች እና ሴቶችን ወደ ሥራ ለማስገባት ታቅዶ ሥራው መጀመሩን ይፋ አድርገዋል።**

በዚህ የከገበሬው የበይነመረብ ግብይት ማስጀመሪያ ሁነት የከገበሬው የምርት አቅራቢዎች ማኔጅመንት Kegeberew Vender Management (KVM) ፣ ብሔራዊ የምርት ስርጭት አገልግሎት (Nationwide Distribution Service-NDS)፣ የስልክ ጥሪ መተግበሪያ (Call Center App-CCA)ን የተመለከተ ሙያዊ ገለጻ በአቶ አማኑኤል መለሰ የፐርፐዝብላክ ኢትዮጵያ የኢኮሜርስ ክፍል ዳይሬክተር የቀረበ ሲሆን በተጨማሪም ለ1 ወር የሚቆየውን የከገበሬው ኢኮሜርስ ማስተዋወቅ ዘመቻ በተመለከተ ማብራሪያ ተሰጥቷል።

የከገበሬው ኢኮሜርስ በመላው አገሪቱ የሚኖሩ ዜጎች ርቀት ሳይገድባቸው ያሻቸውን እንዲገበያዩ ከማስቻሉም በላይ ለማንኛውም የኅብረተሰብ ክፍል በሽያጭ ወኪልነት በመሥራት የገቢ ምንጭ ማግኛ አማራጭ እንደሚሆን ይታመናል።

በበይነ መረብ ግብይቱ የቤት እቃዎች፣ መድኃኒቶች፣ ማሽነሪዎች፣ አልባሳት፣ የኢንዱስትሪ ውጤቶች፣ የግብርና ምርቶች እና ሌሎችም ቁሳቁሶች ለገበያ የሚቀርቡ ከመሆኑ ባለፈ ምርት አከፋፋዮች፣ አምራቾች እና ገዢዎች በአንድ ቦታ የሚገናኙበት ምቹ መገበያያ መድረክ እንደሚሆን ተገልጿል።

## የፐርፐዝብላክ ኢትዮጵያ ማርኬቲንግ ክፍል የኩባያውን የካፒታል አቅም ለማጎልበት ወሳኝ ሚና እንዳለው ተገለጸ።

በተለያዩ የአገራችን ክልሎች በፍራንቻይዝ ሥርዓት በሚያለማቸው እርሻዎች ከሚያመርታቸው እህሎች፣ አትክልትና ፍራፍሬዎች ባሻገር በግብርና ማቀነባበሪያ ክፍሉ የሚዘጋጁ የባልትና እና ኢንዱስትሪ ውጤቶችን በአዲስ አበባ ከተማ ዓድዋ ድልድይ፣ አትላስ፣ ሰሚት፣ አያት፣ ቡልቡላ እና ላፍቶ አካባቢ በከፈታቸው 6 የከገበሬው ሱቆች በተመጣጣኝ ዋጋ ለሸማቾች እያደረሰ የሚገኘው ፐርፐዝብላክ ኢትዮጵያ በማከፋፈያ ሱቆቹ አገልግሎት ለሚሰጡ ሠራተኞች በተለያዩ ጊዜያት የግንዛቤ ማስጨበጫ እና የክህሎት ስልጠናዎችን እንደሚሰጥ ተገለጸ።

ባሳለፍነው ሳምንት ዳሽን ባንክ ለፐርዝብላክ ደንበኞች ያቀረበውን የዳሽን መገበያያ ስጦታ ካርድ አጠቃቀምን በተመለከተ ለሠራተኞቹ የኩባንያው የማርኬቲንግ ክፍል ስልጠና የሰጠ ሲሆን ይህንንም አስመልክቶ የማርኬቲንግ ክፍሉ በዋናነት ኩባንያውን በሚያስተዋውቁ እና አዋጭነት ባላቸው መስኮች በመንቀሳቀስ ከአጋር አካላት ጋር በጥምረት እየሠራ ይገኛል ሲሉ የኩባንያው የማርኬቲንግ ክፍል ዋና ኃላፊ አቶ ታደለ ሰይፉ ተናግረዋል።



ምስል በ ነብዩ ተሾመ

የጥምረት እንቅስቃሴው የፐርፐዝብላክ ኢትዮጵያን ትርፋማነት በማሳደግ ረገድ ትልቅ አስተዋጽዖ እንደሚኖረው የገለጹት ዋና ኃላፊው የደንበኞችን ፍላጎት ለመረዳት የሚያስችል የገበያ ጥናት በማካሄድ ሕብረተሰቡ ስለ ኩባንያው ያለው ግንዛቤ እንዲጨምር የሚያደርጉ በርካታ ተግባራት እየተከናወኑ እንደሚገኙ አስታውሰዋል።

የምርት እና አክሲዮኖች ሽያጭን ከማሳለጥ ባሻገር የከገበሬውን ምርት ተጠቃሚዎች ደንበኝነታቸው ተጠብቆ እንዲቆይ ትልቅ ሚና እየተጫወተ የሚገኘው የፐርፐዝብላክ ማርኬቲንግ ከወራት በፊት በኩባንያው አክሲዮን ሽያጭ እንቅስቃሴ ዙሪያ የዳሰሳ ጥናት ማከናወኑም ይፋ ተደርጓል።

እንደ አቶ ታደለ ገለጻ ፐርፐዝብላክ ኢትዮጵያ በተሳተፈባቸው ልዩ ልዩ መርሐግብራትና በተንቀሳቀሰባቸው አቅጣጫዎች ሁሉ ኩባንያውን የሚያስተዋውቁ የቢልቦርድ፣ ሬዲዮና የሕትመት ሥራዎች በዲፓርትመንቱ በኩል ተከናውነዋል። ልዩ ልዩ ሃይማኖታዊ በዓላትን በማስመልከት መንግሥታዊ እና መንግሥታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች በተሰናዱ ትርኢቶች በመሳተፍ የኩባንያውን ምርትና አክሲዮኖች ከማስተዋወቅ አንጻር ጉልህ አስተዋጽዖ ማበርከቱም ተገልጾ የከገበሬውን ታወር/ሕንጻ ግንባታ አስመልክቶ በተከናወኑት ተግባራት የማርኬቲንግ ክፍል በሙሉ ኃይል መሰማራቱም ተጠቁሟል።

የማርኬቲንግ ክፍሉ ስትራቴጂ እና ጥናት ቡድን ባልደረባ የሆኑት አቶ አቤል አለማየሁ በበኩላቸው ፐርፐዝብላክ ኢትዮጵያ የከገበሬው ታወር ሼር ሆልደር ሞዴልን ለማስተዋወቅ ሲያደርግ የቆየውን የ15 ቀናት ዘመቻ ተከትሎ በተለያዩ የአዲስ አበባ ክፍሎች በሚገኙ ሆቴሎች፣ የንግድ ማእከላት እንዲሁም ሃይፐርማርኬቶች በመሰማራት የተለያዩ ባለሃብቶችን በማምጣት በ1.5 ሚሊዮን ብር የታወር ሼር ሆልደር ሞዴል አክሲዮኖችን ሽያጭ ማከናወን መቻላቸውን ገልጸው በዚህ የአክሲዮን ሥርዓት ዙሪያ በተለያዩ የዓለም ሀገራት የሚገኙ 1,455 ኢትዮጵያውያን ሬስቶራንቶችን ለማነጋገር ታቅዶ ሙሉ ለሙሉ ተግባራዊ መሆኑንም ተናግረዋል።

በታወር ሼር ሆልደር ሞዴል በ90 ቀናት 10 ቢሊዮን ብር ለማሰባሰብ ታቅዶ በተጀመረው እንቅስቃሴ ዘመቻው በተጠናከረ መንገድ የሚቀጥል መሆኑን ይፋ ያደረጉት የማርኬቲንግ ክፍሉ ዋና ኃላፊ አቶ ታደለ ሰይፉ ቀደም ሲል በወርኀ ጥር በተካሔደው የኩባንያው 2ኛ መደበኛ የባለአክሲዮኖች ጉባኤ ውሳኔ መሠረት የኩባንያውን ካፒታል ወደ 100 ቢሊዮን ብር ለማሳደግ የሚሠሩ ሥራዎችንም ማርኬቲንግ ክፍል በቀዳሚነት እንደሚመራ አብራርተዋል።

## ዳሽን ባንክ ለፐርፐዝብላክ ኢትዮጵያ ሠራተኞች የዳሽን ባንክ ስጦታ ካርድ ማቅረቡን አስታወቀ።

ዳሽን ባንክ በሁሉም የከገበሬው ሱቆች ለሚገበያዩ የኩባንያው ሠራተኞች የስጦታ ካርድ ማቅረቡን የፐርፐዝብላክ ዲጂታል አዶፕሽን ማናጀር ወ/ሪት ሩት ጉብሩ ገለጹ።

ፐርፐዝብላክ ከወራት በፊት የዳሽን ባንክ የስጦታ ካርድን ማስተዋወቁን ተከትሎ በዘረጋው ዘመናዊ የክፍያ ሥርዓት የከገበሬውን ደንበኞች የዕለት ተዕለት የግብይት እንቅስቃሴ ቀላል ማድረግ ተችሏል ያሉት ማናጀሯ አሁን ደግሞ ለሁሉም የፐርፐዝብላክ ሠራተኞች ካርዱን ለማዳረስ ማቀዱን አስታውቀዋል።

ካርዱ የደንበኝነት መለያ ቁጥር የያዘ ሲሆን ደንበኞች 1000 ብር እና ከዚያ በላይ ተቀማጭ በተመረጡ የዳሽን ባንክ ቅርንጫፎች ገቢ በማድረግ ማስጀመርና ካርዳቸው ቢጠፋ አልያም በሌሎች እጅ ቢገባ ወደ 8833 STOP ብለው በመላክ በቀላሉ ማቋረጥ ሚችሉ መሆኑም ተገልጿል።

የፐርፐዝብላክ ዲጂታል አዶፕሽን ክፍል የኩባንያውን አገልግሎት በማዘመን ደንበኞቹን ይበልጥ ተጠቃሚ ለማድረግ እና ተደራሽነቱን ለማስፋት የከገበሬው የስጦታ ካርድን ጨምሮ ቴሌ ብር፣ ሳንቲም ፔይ እና ቻፓ የክፍያ መፈጸሚያ መተግበሪያዎች ለደንበኞቹ ያስተዋወቀ ሲሆን ይህም በኩባንያው የኢ-ኮሜርስ (በይነመረብ) ግብይት ላይ ትልቅ አስተዋጽዖ እንደሚኖረው ተጠቁሟል።

የዳሽን ባንክ የስጦታ ካርድ የገና በዓልን በማስመልከት ካርዱን ተጠቅመው በከገበሬው ሱቆች ለሚገበያዩ ደንበኞች ለአንድ ወር ብቻ የሚቆይ የአምስት በመቶ ቅናሽ በማድረግ ወደ ሥራ መግባቱን ያስታወሱት ኃላፊዋ የፐርፐዝብላክ ሠራተኞች ከተመረጡ የዳሽን ባንክ ቅርንጫፎች ከአንድ ሺህ ብር ጀምሮ የፈለጉትን ያህል የገንዘብ መጠን በመሙላት በሁሉም የከገበሬው ሱቆች እንዲገበያዩ እንደሚያስችላቸውም ተናግረዋል።

ኩባንያው ከክፍያ መፈጸሚያ ድርጅቶች ጋር በአጋርነት በመሥራቱ ሊያገኛቸው ከሚችላቸው ጥቅሞች መካከል ለሠራተኞችና ለደንበኞች የሚደረገው የደንበኝነት ቅናሽ አንዱ ሲሆን በቅርቡም ባንኩ ለፐርፐዝብላክ ኢትዮጵያ ሠራተኞች ባቀረበው የስጦታ ካርድ አማካኝነት ላልተወሰነ ጊዜ የሚቆይ ከ2-5 በመቶ ቅናሽ እንደሚያገኙም ገልጸዋል።




ከዚህ ጋር በተያያዘም የከገበሬውን ምርቶች የሚረከቡ ሆቴሎችን ከዳሽን ባንክ ጋር በማገናኘት ከዚህ ቀደም ይሠራበት የነበረውን የአከፋፈል መንገድ አሻሽሎ ለመሥራት መታቀዱም ይፋ ከመደረጉ ባለፈ በኩባንያው የምርት ስርጭት አገልግሎት አማካኝነት ለተለያዩ ተቋማት ተደራሽ ለሚሆኑት የፐርፐዝብላክ የግብርናና የማቀነባበሪያ ምርቶች ተቋማቱ ክፍያ የሚፈጽሙት ምርቱን ከተረከቡ በኋላ በመሆኑ ገንዘብ የመሰብሰብ ሒደቱን አዳጋች አድርጎት መቆየቱ ተጠቁሟል።

ከኩባንያው የትኩረት አቅጣጫዎች አንዱ እና ወቅታዊ የሆነው የከገበሬው ኢኮሜርስን በተመለከተም  እስካሁን ደንበኞች በገበሬው የሞባይል መተግበሪያ የተለያዩ ምርቶችን ግብይት በበይነመረብ እንዲያከናውኑ ሲሠራ መቆየቱንና አገልግሎቱን ይበልጥ ለማዘመን እንዲሁም ከፐርፐዝብላክ ጋር በወኪልነት መሥራት የሚፈልጉ ሰዎች በቀላሉ እንዲመዘግቡ ለማስቻል አዲስ የከገበሬው መተግበሪያ ሥራ መጀመሩን የከገበሬው ኢ. ኮሜርስ  ኃላፊ አቶ አማኑኤል መለሰ አስረድተዋል።

በብሔራዊ የምርት ማከፋፈል አገልግሎት በኩልም የሚደራጁ ማእከላትን ለመቆጣጠር እና ሠራተኞችን ወደ ሥራ ለማስገባት የፐርፐዝብላክ ኢትዮጵያ ኢኮሜርስ እና ዲጂታል አዶፕሽን ክፍሎች በቅንጅት እየተንቀሳቀሱ መሆናቸውንም ተናግረዋል።

## ፐርፐዝብላክ ኢትዮጵያ ከብሔራዊ ደም ባንክ ጋር በመተባበር የደም ልገሳ መርሐግብር አካሄደ።

ሰኔ 19/2015 ዓ.ም የፐርፐዝብላክ ኢትዮጵያ ከፍተኛ የሥራ ኃላፊዎችና ሠራተኞች ከብሔራዊ ደም ባንክ በመጡ የህክምና ባለሞያዎች አማካኝነት በኩባንያው ዋና መሥሪያ ቤት በፈቃደኝነት ደም ለግሰዋል።

በመርሐግብሩ የኩባንያውን ዋና ሥራ አስፈጻሚ ጨምሮ የኩባንያው ከፍተኛ የሥራ ኃላፊዎችና ሠራተኞች በፈቃደኝነት ደም የለገሱ ሲሆን "በለገስነው ደም የአንድ ሰው ሕይወት ማዳን በመቻላችን ደስተኞች ነን" ሲሉ ስሜታቸውን አስረድተዋል።

ምስል በ ነብዩ ተሾመ



> “
> የኩባንያው ዋና ሥራ አስፈጻሚ ዶ/ር ፍስሐ እሸቱ የደም ልገሳው እንደግልም ሆነ ለኩባንያው 2ኛ መሆኑን የገለጹ ሲሆን ፐርፐዝብላክ ለትርፍ የተቋቋመ የንግድ ድርጅት ከመሆኑም ባሻገር ከ20 ሺህ ያላነሱ ባለአክሲዮኖች እንዳሉት የሕዝብ ተቋም ደም በመለገስ ማኅበራዊ ኀላፊነቱን እየተወጣ ይገኛል ብለዋል።

የብሔራዊ ደም ባንክ አገልግሎት ባልደረባ የሆኑትና ለ 93 ጊዜ ደም በመለገስ የሚታወቁት ሲስተር አሰጋሽ ጎሳ በበኩላቸው ከቀናት በፊት ለኩባንያው ሠራተኞች የግንዛቤ ማስጨበጫ መስጠታቸውን በማስታወስ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የተከሰተውን የደም ክምችት እጥረት ለመቅረፍ በሁሉም የመንግሥት እና የግል ድርጅቶች፣ የሃይማኖት ተቋማት እና ማኅበራዊ እንቅስቃሴዎች ዜጎች በነቂስ ወጥተው ደም በመለገስ የወገናቸውን ሕይወት ሊታደጉ ይገባል ሲሉ ጥሪያቸውን አስተላልፈዋል።

ምስል በ ነብዩ ተሾመ



እድሜው ከ18-68 የሆነና ክብደቱ ከ45 ኪሎ ያላነሰ ማንኛውም ሰው በ አመት ለ4 ጊዜ በየ3 ወሩ ደም መለገሥ ይችላል ያሉት ባለሙያዋ የደም ግፊት፣ የሚጥል በሽታ እና የሌሎች በሽታዎች መድሃኒት በቋሚነት የሚወስዱ ሰዎች ደም መለገስ የማይችሉ ሲሆን በፈቃደኝነት ደም ለመለገስ የሚመጣ ማንኛውም ለጋሽ አራቱን የደም ምራመራዎች ማለትም ኤች ይ ቪ፣ ሄፒታይተስ ቢ እና ሲ እንዲሁም  ደግሞ የደም አይነት ልየታ በነጻ እንደሚደረግለት ተናግረዋል።

በመጨረሻም የፐርፐዝብላክ ኢትዮጵያ በጎ ፈቃደኛ ደም ለጋሾች በፈቃዳቸው በለገሱት ደም በወሊድ፣ በተለያዩ አደጋና በሽታዎች ምክንያት ደም የሚፈሳቸውን ወገኖች ሕይወት ለመታደግ የሚያስችል አስተዋጽዖ በማድረጋቸው ክብር ይሰማናል ያሉ ሲሆን በቀጣይም በመሰል መርሐግብሮች በቋሚነት በመሳተፍ ማኅበራዊ ኃላፊነታቸውን እንደሚወጡ አስታውቀዋል።

## የፐርፐዝብላክ ኢትዮጵያ ጠቅላላ አገልግሎት ክፍል የኩባንያውን ንብረቶች ከመጠበቅ አንጻር ልዩ ልዩ እንቅስቃሴዎችን እያከናወነ እንደሚገኝ ተገለጸ።

የኩባንያውን የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴ በማሳለጥ የፐርፐዝብላክ የጀርባ አጥንት ሆኖ እየሠራ የሚገኘው የጠቅላላ አገልግሎት ክፍል የተቋሙን የፋይናንስ ምንጮች ለማስፋት በተጀመሩ እንቅስቃሴዎች ሁሉ ግንባር ቀደም ተሳታፊ ነው ሲሉ የክፍሉ ኃላፊ አቶ ብሩክ በነበሩ ገልጸዋል።

ክፍሉ ለኩባንያው ተጨማሪ የገቢ ምንጭ ለማስገኘት የዋና መሥሪያ ቤቱን አዳራሽ ከማከራየት አንስቶ የንብረት እና ወጪ ብክነትን ለመቀነስ በርካታ ዕቅዶችን ነድፎ እየተንቀሳቀሰ የሚገኝ መሆኑን እንዲሁም ከጥበቃና ጽዳት አገልግሎት ጀምሮ የተሽከርካሪዎችን ስምሪት አቅርቦት እንዲሁም የኪራይ እና ግዢ ጉዳዮችን በንቃት እያከናወነ እንደሚገኝ ኃላፊው ተናግረዋል።

> “
> እንደ አቶ ብሩክ ገለጻ ክፍሉ ለቋሚ ንብረቶች የኩባንያውን መለያ ቁጥር በመስጠት ለተጠቃሚዎች በማስረከብ ሠራተኞች እያንዳንዳንዱን ንብረት በተጠያቂነት ስሜት እንዲጠቀሙ ከማድረግ ባለፈ ለነባርና በአዲስ መልክ ለሚቋቋሙ የሥራ ክፍሎች አስፈላጊውን መገልገያ ከማሟላት በተጨማሪ በዋናው መሥሪያ ቤት፣ በምርት መጋዘን እንዲሁም በከገበሬው ሱቆች የሚገኙ ንብረቶችን ወጪና ገቢ ለመቆጣጠር በየወሩ ቆጠራ እንደሚያካሒድ በተጨማሪም ከተለያዩ ክፍሎች ለሚመጡ እቃዎች ግዢና ተያያዥ ጥያቄዎች አፋጣኝ ምላሽ መስጫ መንገዶችን እንደሚከተል አብራርተዋል።

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ለተሽከርካሪዎች ኪራይ የሚወጣውን ከፍተኛ ወጪ ለመቀነስ በማሰብ ለግብርና፣ ጭነት እና ሌሎችም በኩባንያው የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴ አገልግሎት የሚሰጡ ተሽከርካሪዎችን በመግዛት ለመኪና ኪራይ የሚወጣውን ወጪ መቀነስ ተችሏል ያሉት ኃላፊው የፍተሻ ጊዜያቸው የደረሰ መኪኖች አስፈላጊው ጥገና እንዲደረግላቸው የማድረጉ ተግባርም በዚሁ ክፍል አማካኝነት እንደሚከወን አስታውቀዋል።

ከዚህ ጋር ተያይዞም ቀደም ሲል በብልሽት ጊዜ ባለሞያ እስከሚገኝ ይፈጠሩ የነበሩ ክፍተቶችን ለመድፈን እና በተፈለገው ጊዜ ጥገና እንዲደረግ ለማስቻል ለኤሌክትሪክ እና ተያያዥ ንብረቶችን ጥገና በቅጥር ሠራተኞችን ወደ ተግባር ማስማራቱ በአማራጭነት የተጠቆመ ሲሆን በቀጣይም ለኩባንያው ተሽከርካሪዎች ጥገና የሚሰጥ ጋራዥን ጨምሮ ሌሎችንም አገልግሎት ሰጪ ዘርፎችን ለማቋቋም መታቀዱን ኃላፊው ገልጸዋል።

ኩባንያው በልዩ ትኩረት እየሠራባቸው የሚገኙት የከገበሬው ሕንጻ፣ የከገበሬው ኢኮሜርስ እና ከገበሬው ቴሌቪዥንን በተመለከተ አቶ ብሩክ የፕሮጀክቶቹን ግዝፈት እና ወቅታዊነት ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት በአላቂ እቃዎች እና ቋሚ ንብረቶች ግዢ ዙሪያ አስፈላጊውን ለማድረግ እንቅስቃሴዎች መከናወናቸውን ጠቁመው የጠቅላላ አገልግሎት ክፍሉ በዋናው መሥሪያ ቤት ለከገበሬው ቴሌቪዥን፣ ከገበሬው ህንጻ እና ሌሎች አገልግሎቶች የሚውል 1362 ካሬ ቦታ መከራየቱን እንዲሁም በ15 ቀናት ውስጥ ተረክቦ አስፈላጊውን ቅድመ ዝግጅት እንደሚያጠናቅቅም አስታውቀው የከገበሬው ኢኮሜርስ ሦስት የተለያዩ ፕሮጀክቶችን በይፋ ማስጀመሩን ተከትሎም ለጥሪ ማእከል ግንባታ የአስፈላጊውን እቃ ግዢ እና ዝርጋታ በስኬት ማጠናቀቅ መቻሉንም ገልጸዋል።

ዋና አዘጋጅ፥ ሰላማዊት ደበበ
ሲነየር ሪፖርተር፥ ጌታባለው ገ/ሐና
ሪፖርተር፥ ኤደን ደነቀ

## ለበለጠ መረጃ

ሰንጋተራ ነጋዴዎች ህብረት ህንጻ 5ተኛ ፎቅ
+251-946-545454/
+251-925922222/
+251-925822222
7151
www.purposeblackethiopia.com